# ኅብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም የግጭት መንስኤ ወይስ መፍትሄ

*“ዋና የደኅነታችን ስጋት የውስጥ ስጋት ነው፡፡ ድህነት ተስፋፍቶ እንዳንበታተንና እንዳንተላለቅ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጠፍቶ ለእልቂት እንዳንዳረግ ነው፡፡ ይህንን ዋነኛ ስጋት ማስወገድ የሚቻለው ድኅነትን በማስወገድ በኢኮኖሚያዊ ርብርብና ልማት ነው፡፡”*

*(የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደኅንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ገጽ25)*

አጥኚዎችም ፖለቲከኞችም ግጭት በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ብርቅም ድንቅም ያልሆነ የተለመደ ጉዳይ እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ በአንድ አገር ህዝብ ውስጥ በሀሳብ ልዩነቶች አልያም በይገባኛል ጥያቄዎች ምክንያት በተለያዩ ማኅበረሰቦች መካከል የሚፈጠረውን ዓይነት ግጭት ማለት ነው፡፡ አቶ በረከት ስምዖን በመጽሐፋቸው ላይ ስለ አፍሪካ ቀንድ ሀገራት እንዲህ ይላሉ፡-

> *“ሲፈርድብን የምንኖረው በተተራመሰው የአፍሪካ ቀንድ ነው፡፡ በዓለማችን እጅግ አስከፊ የግጭት ቦታዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ይኸው የአፍሪካ ቀንድ የሚባለው የእኛው ቀጠና ነው፡፡ በቀጠናችን ልዩነቶች በሰላም የሚፈቱበት ባህል የተለመደ አይደለም፡፡ለትንሹም ለትልቁም ጠመንጃ መማዘዝ የቀለለው መፍትሔ ነው፡፡ በመሬት፣ በግጦሽና በውኃ ቦታ የተነሳ፣ በማንነት ጥያቄ የተነሳ፣ ወይም ደግሞ በዴሞክራሲና በኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ምክንያት የሚቀሰቀስ ግጭት ሞልቶ የተረፈበት አካባቢ ቢኖር ይኸው የእኛው የአፍሪካ ቀንድ ነው፡፡”* (በረከት ስምዖን፣ 2003. የሁለት ምርጫዎች ወግ፡ ናዳን የገታ አገራዊ ሩጫ፡፡ ገጽ 15)

አገራችን በዚህ ግጭት ሞልቶ በተትረፈረፈበት ክፍለ አህጉር ውስጥ እንደመገኘቷ በውስጥም በውጭም መጠነ ሰፊ ግጭቶች አሳልፋለች፤ እያጋጠማትም ይገኛል፡፡ በአገራችንም ሆነ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በውጫዊ ምክንያት ከሚፈጠረው ግጭት ይልቅ ውስጣዊ ግጭቱ የበለጠ አገራቱን  እየጎዳቸው እንደሚገኝ አሁን አገራቱ ያሉበት የእድገት ደረጃና ወቅታዊ ሁኔታቸው አንዱ ማረጋገጫ ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ ነባራዊ ሁኔታ አፈንግጣ ለመውጣትና በኢኮኖሚና በፖለቲካው ዘርፍ ንቁ ተሳትፎ ያለውና ተጠቃሚነቱን ያረጋገጠ ማኅበረሰብ ለመፍጠር በመትጋት ላይ ከሚገኙ አገራት አንዷ ነች፡፡ በዚህ ጥረትም አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት ይታይባቸዋል ከሚባሉት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት አንዷ የመሆን ግብን አሳክታለች፡፡ ይህ ማለት ግን ከውስጣዊ ግጭት ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆነ ሀገር ተመስርቷል ማለት አይደለም፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ብቻ ሳይሆን ቆየት ያለ ባህሪ ያላቸው በህዝቦች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች አሁን ድረስ አገራችን ውስጥ ይከሰታሉ፡፡

የሀገራችን የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደኅንነት ስትራቴጂ “ለአገራዊ ጥቅማችንና ህልውናችን ዋነኛው አደጋ ድኅነታችን፣ ኋላቀርነታችንና የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥርዓታችን ስር አለመስደድ ነው” ይላል፡፡ መንግሥትም በዚህ ወቅት በአገራችን  የሚከሰቱ ግጭቶችን በአመራሩ ውስጥ ያለ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የወለደው የመልካም አስተዳደር ችግር እንደሆነ በተደጋጋሚ ይናገራል፡፡ በእርግጥ አገራችን ውስጥ ስለሚታዩ ግጭቶች ስንጽፍ ግልጽ መሆን ያለባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው ጉዳይ የግጭት ምክንያቶች ላይ ያለው የአሰላለፍ ልዩነት ነው፡፡

የመጀመሪያው አሰላለፍ ውስጣዊ ግጭቶችን የወለዳቸው የምንከተለው የኅብረ ብሔር ፌዴራሊዝም የመንግሥት ስርዓት እንደሆነ አድርገው የሚቆጥሩ ግለሰቦችና የፖለቲካ ቡድኖች አሉ፡፡ በዚህ እሳቤያቸው መነሻነትም አገራችን የምትከተለው ህብረ ብሔራዊ የፌዴራሊዝም ስርዓት ዋናው የችግሩ ምንጭ መሆኑን ያሰምሩበታል፡፡ በዚህ አስተሳሰብ ላይ ተመስርተውም ብዙዎቹ ጠቅላላ የሆነ መልስ ይሰጣሉ፡፡ “የቦታ አቀማመጥን መሰረት ያደረገ (ጂኦግራፊያዊ) ፌዴራሊዝም ግጭቶች እንዳይከሰቱ ለማድረግ የተሻለ ስርዓት ነው” ይላሉ፡፡

ሁለተኛው ጎራ ደግሞ አሁን አገራችን ላይ የሚታዩ ግጭቶች ምክንያታቸው የፌዴራሊዝም ስርዓቱ በራሱ የወለዳቸው ሳይሆን የዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ስር አለመስደድ የወለደው የመልካም አስተዳደር ችግርና በእነዚህ አካባቢዎች ያለ ድህነትና የተፈጥሮ ኃብት ሽሚያ ናቸው የሚል ነው፡፡

ማንኛውም የመንግሥት ስርዓት የራሱ የሆነ ደካማ ጎን ሊኖረው እንደሚችል የሚታወቅ ቢሆንም የመንግሥት ስርዓቶች በራሳቸው ግን የግጭት ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይልቁንም በምስራቅ አፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶች ምክንያታቸው ከዚህ የተለየ እንደሆነ አጥኝዎች ይስማማሉ፡፡ ኮሌርና ሆፍለር የተባሉ አጥኝዎች በ1998 ዓ.ም ባወጡት On economic cause of civil war በተባለ የጋራ ጥናታቸው ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች (ወይም በጥቅሉ ድህነት) ዋናው በህዝቦች መካከል ያለ የግጭት ምክንያት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ክላር የተባለው አጥኝ ደግሞ በ በ2001 ባሳተመው ጥናቱ የአብዛኛው አፍሪካውያን የግጭት ምክንያት የተፈጥሮ ኃብት ይገባኛል ጥያቄ መሆኑን ይናገራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሀንቲንግተን የተባለ አጥኝ በ1993 ዓ.ም. (እ.ጎ.አ.) The clash of Civilization በተሰኘ ጥናቱ የተለያዩ ባህሎችን በአንድ ላይ ለማኖር በሚሞከርበት ጊዜ የሚፈጠር አለመግባባትና የማንነት ጽንፈኝነት (ጠባብነት) ለግጭት የሚያጋልጥ ሁነኛ ምክንያት እንደሆነ በጥናቱ አረጋግጧል፡፡

እነዚህ (ድህነት፣ የተፈጥሮ ኃብት የይገባኛል ጥያቄና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎችን በአግባቡ አለመመለስ) ከሌሎችም ተጨማሪ ምክንያቶች ጋር በእኛ የአፍሪካ ቀንድ ቀጠና የሚታወቁና በጥናት የተረጋገጡ የግጭት ምክንያቶች መሆናቸውን ምሁራኑ ይስማሙበታል፡፡ በአጥኚዎች መሰረትም ህብረ ብሔራዊ የፌዴራል ስርዓት የግጭት ምንጭ ከመሆን ይልቅ በተቃራኒው የግጭቶች መፍትሔ እንደሆነ ከላይ የጠቀስነው ሀቲንግተን (1993) የተለያዩ ማንነቶችን በአንድ ላይ ለማኖር መሞከር የማንነት ጭቆናን ስለሚፈጥር የግጭት ምክንያት እንደሚሆን ጠቅሷል፡፡ ስለዚህ እንዲህ ዓይነት የግጭት ስጋቶችን ለመፍታት ዜጎች ራሳቸውን በራሳቸው ሊያስተዳድሩበት የሚችሉበትንና የማንነት ጥያቄዎቻቸው የሚፈቱበትን የመንግሥት ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ ዋና መፍትሔው ነው፡፡ ስለዚህ የህብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ በራሱ የግጭቶች ምክንያት ነው የሚለው አሰላለፍ ውድቅ ነው፡፡

ሁለተኛው ቁምነገር ደግሞ ህብረ ብሔራዊ የፌዴራል ስርዓቱ መንግሥት አልያም አንድ የፖለቲካ ድርጅት ፈልጎት በህዝቦች ላይ በግዴታ የጫነው ቀንበር አይደለም፡፡ የፌዴራል ስርዓቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የፍላጎትና የትግል ውጤት ነው፡፡

ከ1953ቱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ የተደረገ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ከተፈጠረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጀምሮ በአገራችን የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች መብታቸው ተሟልቶ ይከበር ዘንድ ገበሬውም የተማረውም ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ ትግል አድርጓል፡፡ በተለይ ተማሪው በተከታታይ ባደረገው ትግል ለብሔር ብሔረሰቦች መብት መከበር የሚታገሉ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች መመስረት ችለው እንደነበር ታሪክ ያስቀመጠው ሀቅ ነው፡፡ ህብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ኢህአዴግ ፈልጎት በህዝቦች ላይ የጫነው ህገ ወጥ ስርዓት ሳይሆን ዜጎች ማንነታቸው ታውቆና ተከብሮ ወደው የሚቀበሏት አንዲት የጋራ ሀገር እንዲኖራቸው ሽተው ያመጡት ስርዓት ነው፡፡

ለዚህ ማሳያ የሚሆነን በተማሪዎች እንቅስቃሴ የመጀመሪያ ዓመታት ለውጡን በመምራት ከሚታወቁት ወጣቶች አንዱ የነበረው ዋለልኝ መኮንን ነው፡፡ ይህ ወጣት የተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪ በኅዳር 1969 ዓ.ም. “On the Question of Nationalities in Ethiopia” በተባለው መጣጥፉ ላይ ብሔርን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ ለአገራችን እንደሚያስፈልግ ሞግቶ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡

> *ዋለልኝ በጽሁፉ፡- “አሁኑኑ ጭቆናውን ልናስቆመውና ፍትሀዊ የሆነ የህዝቦች መንግሥት ልናቋቁም ይገባል፡፡ ፍትሀዊ የሆነ የህዝቦች መንግሥት ምንድን ነው? ሁሉም ብሔሮች በአገራቸው ጉዳይ በእኩልነት የሚሳተፉበት ማለት ነው፡፡ ሁሉም ብሔሮች ቋንቋቸውን፣ ሙዚቃቸውን፣ ታሪካቸውን የሚጠቀሙበትና የሚያሳድጉበት እድል በእኩልነት ሊያገኙ ይገባል ማለት ነው፡፡ አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሞ፣ ሀረሪ፣ ሶማሌ፣ ወላይታ፣ ጉራጌ፣...ወዘተ በእኩልነት ሊስተናገዱና ሊገለገሉ ይገባል ማለት ነው፡፡ ፍትሀዊ የሆነ የህዝቦች መንግሥት ማለት አንድም ብሔር የምጣኔ ኃብትም ሆነ የባህል የበላይነትና ጭቆና በሌሎች ብሔሮች ላይ የማያደርስበት ሀገር መመስረት ማለት ነው፡፡” ይላል፡፡*

በዋናነት ዋለልኝ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባና ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በውስጧ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች የጋራና ተፈቃቅደው ተከባብረው ሊኖሩባት የምትገባ ሀገር እንደሆነች ጽፏል፡፡ አንድነትን ሽፋን አድርጎ በሌሎች ብሔሮች ላይ የሚደረገው ባህልን፣ ታሪክን፣ ቋንቋን፣…የመሳሰሉ የማንነት መገለጫዎችን መጨፍለቅና ማጥፋት እንዲሁም የኢኮኖሚና የባህል ወረራ በማድረግ ዜጎችን ማንነት ማሳጣት እስካልቆመ ድረስ ይህች ሀገር እንደሀገር መቀጠል እንደማትችል በዘመኑ ለነበረው ወጣትም ለስርዓቱም አሳይቷል፡፡

ዋለልኝን እንደማሳያ ወሰድን እንጂ ሌሎችም በተናጠልና በተደራጀ አካሄድ በዚህ ዓይነት መንገድ ታግለዋል፡፡ ለአብነት የኢህአዴግ እህት ድርጅት የሆነው ህወኃት እንኳን ሳይመሰረት በፊት ብዙዎች የጻፉለትና አምቦ ላይ በ1955 ዓ.ም የተመሰረተው የኦሮሞን የብሔርተኝነት ጥያቄ ይዞ የተነሳው የሜጫና ቱለማ ማኅበር ዋና ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ማኅበር ኦላና ዞጋ የተባለው አጥኚ በ1993 ዓ.ም ባወጣው "ግዝትና ግዞት፡ ሜጫና ቱለማ መረዳጃ ማኅበር" በተሰኘው ጥናታዊ ስራው እንደሚያትተው ሜጫና ቱለማ ማኅበር "የብሔርተኝነት ጥያቄ የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ላይ ይጥለዋል" ተብሎ በሚታመንበት በንጉሡ ዘመን የኦሮሞን ህዝብ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋን ለማሳወቅ ከፍተኛ ጥረት እንዳደረገ ያስገነዝባል፡፡ ብዙ ዓመታትን የወሰዱት የእነዚህና ሌሎች መሰል ትግሎች ውጤት ነው ህብረ ብሔራዊ የፌዴራል ስርዓቱን የህዝብ ሥርዓት አድርጎ የወለደው፡፡

ስለዚህ ህብረ ብሔራዊ የፌዴራል ስርዓቱ የግጭት ምክንያት መሆኑ ቀርቶ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተደጋግፈውና ተከባብረው አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ይበጀናል ብለው የመረጡት የስርዓት አማራጭ ነው፡፡

የፌዴራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር የግጭት መከላከልና አፈታት ዳይሬክቶሬት ጀነራል በ2004 ዓ.ም ባሳተመው የሰላም እሴት ግንባታ ሞጁል ላይም አገራችን ውስጥ የሚከሰቱና አሁን እየታዩ ያሉትን ውስጣዊ ግጭቶች አስመልክቶ አራት ዋና ዋና ምክንያቶች እንዳሏቸው ያብራራል፡፡ እነዚህም የመሬትና ሌሎች የተፈጥሮ ኃብቶች ይገባኛል ጥያቄ፣ የኢኮኖሚ ችግር፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና ከአመራር አቅም ጋር የተያያዙ ክፍተቶች ናቸው፡፡

ይልቁንም የግጭትን ምክንያት አገሪቱ ከምትከተለው የህብረ ብሔር ፌዴራሊዝም ስርዓት ጋር ሊያያይዘው የሚችል ችግር አለ ከተባለም ስርዓቱን በትክክል አውቀውትና ተረድተውት ለራሳቸውና ለጎረቤት አስተዳደር በአግባቡ መጠቀም ያልቻሉ አካባቢያዊ አመራሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ ብቻ ነው፡፡ ከላይ የአመራር አቅም ጋር የተያያዙ ክፍተቶች ያልነው አንዱ ይህ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ መፍትሔው የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ሳይሆን የህዝቦችን በመግባባትና በመከባበር እንዲሁም በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተ የራስ አስተዳደርን በጥብቅ መሰረት ላይ ማቆም አንዱ ነው፡፡

እነዚህንና ከላይ የገለጽናቸውን ምክንያቶች ከመሰረታቸው ማየት አንዳንዶቹ እንደሚሉት ግጭት ህብረ ብሔር የፌዴራሊዝም ስርዓቱ የወለደው በሽታ አለመሆኑን ለመረዳት ያስችሉናል፡፡

አገራዊ ጥቅማችንንና ህልውናችንን ለማስጠበቅ በዋነኝነት በአገር ውስጥ በሚካሄድ ርብርብ እነዚህን የስጋት ምንጮች ማድረቅ እንደሚገባ ግልጽ ነው፡፡ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደኅንነት ፖሊሲያችን እንደሚያስቀምጠውም ዋና የስጋት ምንጮች ተብለው የተለዩትን (ድህነት፣ ስር ያልሰደደ የዴሞክራሲያችን እድገትና የመልካም አስተዳደር ግንባታ) ማነቆዎችን በህዝብ ተሳትፎ ለመፍታት መረባረብ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡

የግጭቶች መከሰት በራሱ አገራችንን ያልተረጋጋች ሊያደርጋትና ሊያስብላትም አይችልም፡፡ ግጭት የዳበረ ዴሞክራሲ ባላቸው አገሮችም ውስጥ ቢሆን ሊፈጠር ይችላል፡፡ ትልቁ ጉዳይ ያለው ግን ግጭቶች ሲፈጠሩ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የሰው ህይወትና የንብረት ውድመት ሳያስከትሉ የመፍታት ብቃትን በአመራሩ ዘንድ መገንባት መቻልና አለመቻሉ ላይ ነው፡፡ ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ እንደየአካባቢዎች ነባራዊ ሁኔታ ግጭቶችን እያጠኑ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት መቻሉ ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ዋና ዋና ጉዳዮች የፌዴራል መንግሥትና የየአካባቢውን አመራሮቻችን አቅም ግምት ውስጥ አስገብተው የሚሰሩ በመሆናቸው ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

የግጭት ወረዳና ቀበሌ ተብለው በተለዩ የአገራችን አካባቢዎች በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ችግሮችን ለመፍታት መስራትና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት መፍታት ባህሉ የሆነ ማበረሰብ ለመፍጠር ተግቶ መስራት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ

አይደለም፡፡ ምክንያቱም የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደኅንነት ፖሊሲው እንዳስቀመጠው ከውጫዊ ስጋት በበለጠ ዋናው የህልውናችንና የደኅንነታችን አደጋ የውስጥ ግጭት ስለሆነ ነው፡፡

ይህንን ለማሳካት ትልቅ ርብርብ ያስፈልጋል የምንልበት ምክንያትም አሁን አገራችን ላይ እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶች ሁሉ ስረ መሰረታዊ ምክንያቶቻቸው በአጭር ጊዜ የማይፈቱ ሰፊ ትግል የሚጠይቁ የረዥም ጊዜ ስራዎች መሆናቸው ነው፡፡ ድህነትን ማሸነፍና ፍትሀዊ የህዝቦችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የዴሞራሲና የመልካም አስተዳደር ስርዓትን መገንባት፣ የአመራሩን የአቅም ክፍተት በመሙላት ብቃቱ የተረጋገጠ የየአካባቢው አመራር መፍጠር እና አለመግባባቶችን በዴሞክሲያዊ (ሰላማዊ) መንገድ መፍታት ባህሉ የሆነ ማኅበረሰብ መፍጠር በአንድ ጀንበር የሚሳኩ ሳይሆኑ የሁላችንንም መጠነ ሰፊ ትግል የሚጠይቁና በሂደት እየተገነቡ የሚሄዱ ናቸው፡፡

በአገራችን ለዘመናት የተገነባ ጥልቅ መሰረት ያለውን ድህነት ለመግታት እየታየ ያለው ተስፋ ሰጭ እድገት በአመራሩ ብቃት የመጣ መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ይህም በየደረጃው ያለ የአመራር አቅምን በማሳደግ ግጭቶችን ከስር መሰረታቸው በመፍታት ሰላሟ የፀና ሀገርን ለመጪው ትውልድ ማስረከብ እንደምንችል የሚያስረግጥ ነው፡፡

በፌዴራልና አርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር

የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት